ስለ መጨረሻ ጊዜ ሲወራ ብዙ ሰዎች በጣም ይፈራሉ በተለይ የዳንኤል እና ራዕይ መጽሐፍ ማንበብ በጣም ያስፈራቸዋል። ነገር ግን መሆን ያለበት ተቃራኒው እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል "ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ። **ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።**"ራዕ 1:1-3 እንዲሁም ክርስቶስ ስለ መጨረሻ ጊዜ ሲናገር በማቴ 24:15 እንዲህ ይላል "እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ **አንባቢው ያስተውል**" ይላል። በመጨረሻ ዘመን ላይ የምንገኝ ሰዎች በተለያዩ ማታለያዎች እንዳንታለል መጠንቀቅ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ሰይጣን "እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል።" ራዕ 13:13 ይህም የአጋንንት መንፈስ ነው። ራዕ 16:14 ይላል።

ወንድሞቼ ሆይ በዚህች አጭር ጹሁፍ ስለ መዝሙር (ሙዚቃ) እና ስለ አምልኮ በማንሳት ከመጻሐፍ ቅዱስ እናጠናለን።

አንድ ቤት ከሩቅ ሆነን ብንመለከት የቤቱ መሰረት አይታየንም ስለዚህ መሰረቱ ከሩቁ ስላልታየን ያ ቤት መሰረት የለውም ብለን መደምደም እንችላለን? ልክ እንደዚው አንድ መዝሙር የመዝሙሩ ዜማ ደስ ስላለን ወይም ዘማሪውን ስለምንወደው ወይም ደግሞ የሙዚቃ መሳሪያው ደስ ስላለን መዝሙሩ ጥሩና እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነው ብለን መደምደም አንችልም። ሌላ ምሳሌ እንውሰድ ጦርነት የሚደረገው በጦር ሜዳ ላይ ነው እንዲሁም የጦርነቱን እንዴት እንደሚዋጉ የሚወስነው የጦር ሜዳው ነው። በሌላ አባባል የጦርነቱን ውጤት የሚወስነው ጦርነቱ የሚካሄድበት ሜዳ ነው። ይህ ጦርነት የአምልኮ ምሳሌ አድርገን መውሰድ እንችላለን ሜዳውን ደግሞ የሚያመክተው ለእግዚአብሔር ያለንን ዕይታን ይወክላል።

የሙዚቃ ጥቅም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሷል። በአግባቡና በትክክለኛ ሁኔታ ከተጠቀምንበት ለእግዚአብሔር ውድ የሆነ ስጦታ ና ሃሳብን እንዲሁም ነፍስን ከፍ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር እንድትመለከት የሚያደርግ ነው። *Education,167,168*

እንዲሁም ሙዚቃ ስሜታችንን የመቆጣጣር ባህሪይ አለው ስለዚህ ስናዝንና ስንደሰት ስሜታችንን ለመግለጽ መዝሙርን እንጠቀማለን። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስም ይህንኑ ያደርግ ነበረ።

እየሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ በመዝሙር ፈተና ደስዖበታል። አከባቢው በጭንቀት ፤ በፈርሃት እና በጥርጣሬ የተነሳ በጨለማ ሲከበብ የምስጋናና የእምነት መዝሙር ከአንደበቱ ይሰማ ነበረ። *Education, 166*

መዝሙር ተስፋ መቁረጥን የምናሸንፍበት መሳሪያ ነው። ልባችንን ብርሃን ወደ ሆነው ወደ አዳኛችን ስናቀርብ ለሰውነታችን በረከትና ጤንነትን እናገኛለን። *Ministry of Healing* p. 254. (1905)

አለማዊ ጭንቀት ለሰማያዊ ነገር ጊዜ እንዲያጣ አላደረገውም። ብዙ ጊዜ ዜማዎችን በማዜምና ሰማያዊ መዝሙሮችን በመዘመር የልቡን ደስታ ይገልጽ ነበረ። ብዙ ጊዜ ድምጹን ከፍ አድርጎ እግዚአብሔርን ሲያወድስና ሲያመሰግን የናዝሬት ነዋሪዎች ይሰሙት ነበረ። በዝማሬ ከሰማይ ጋርግንኙነት ነበረው። ጓደኞቹ ሥራ አድክሟቸው ሲማረሩ ከከንፈሩ በሚወጣው ጣፋጭ ዜማ ይረኩ ነበረ። የእርሱ ውዳሴ ክፉ መናፍስትን አስወግዶ እንደ ዕጣን ቦታውን በመዓዛ ይሞላው ነበረ። የአድማጮቹ ህሊና ከምድራዊ ግዞት ወጥቶ ወደ ሰማያዊው ቤት ይመጥቅ ነበረ። (ዘመናት ምኞት 57,58 በአማርኛ)

ወደ አለም ፍጻሜ እየተቃረብን ስንሄድ የክርስቶስን ዳግም ምጻት ስንጠባበቅ ሳለ በእግዚአብሔር ህዝብ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ፍላጐት እየተነሳሳ ይሄዳል። ሆሴ 6:3, ዘካ 10:1, ያዕ 5:7

ሰይጣንን ከሚያነድዱትና ከሚስቆጡት ነገሮች ውስጥ አንዱ ትክክለኛ የሆነና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አምልኮ ነው። ሰይጣን ከሰማይ ከመውደቁ በፊት ፍጹም በሆነ አከባቢ እግዚአብሔርን ያመልክ ነበር። እንዳውም የመዘምራን (ኳየር) መሪ ነበረ። ስለዚህ ምን አይነት የአምልኮ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ተጠንቅቆ ያውቃል። ወገኖቼ ሆይ ሰይጣን ከሰማይ የተጣለው በአምልኮ ጉዳይ እንደሆነ ታውቃላችሁ? 'አምልኮ ይገባኛል' የሚል አጉል ኩራትና ትዕቢት በውስጡ ስላደረበት ነው።

ስለዚህ ሰይጣን በመጨረሻ ዘመን ላይ የምንገኝ የእግዚአብሔር ህዝቦችን እንዴት አድርጎ እንደሚያስት ጠንቅቆ ያውቃል። ይህንን መረዳት የምንችለው ግን የእግዚአብሔርን ቃል በትጋትና በፀሎት ስናጠና ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትክክለኛ አምልኮና ስለሙዚቃ በግልጽ ያስቀምጣል። በዚህ ጥናታችን ይህንኑ ርዕስ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከትንቢት መንፈስ ጠለቅ ብለን ለማየት እንሞክራለን።

በመጀመሪያ የመዝሙር አገልግሎትን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ የተፃፉትን እናጠናለን። በብሉይ ኪዳን ውስጥ መዝሙር ለተለያዩ ጥቅሞች ላይ ውሏል።

- በዘፍ 31 ላይ ለያዕቆብ በተዘጋጀ ድግስ ላይ
- በዘፀ 15 ላይ እስራኤላዊያን ቀይ ባህርን ሲሻገሩ
- በመሳ 11:34 ላይ ዮፍታሄ ከጦርነት ሲመለስ
- በ1ሳሙ 18:6 ላይ ዳዊት ሲያሸንፍ
    - በ1ሳሙ 22 ላይ አህዛብ ለእግዚአብሔር ክብር ሲሰጡ
- በ1ዜና 16:18-10 በአሳፍ የተጻፈ መዝሙር በዳዊት ሲቀርብ
- በኢዮ 36 አንድ ሰው እግዚአብሔርን ስለ ስራው ሲያወድስ
- ኢሳ 42 ህዝቡን ለእውነተኛ አምልኮ ሲያነሳሳ
- በዮናስ 2:10 ዮናስ ከአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሲወጣና ሲያመሰግን::

ሙዚቃ ለአምልኮ፣ ንጉስ ሲነግስ፣ ንጉስ ድል አድርጐ ሲመለስ፣ የተማረከው የእግዚአብሔር ታቦት ሲመለስና ለተለያዩ ጉዳዮች ስራ ላይ ውሏል:: ነግር ግን ለአምልኮ የሚቀርበው መዝሙር አብዛኛው ጊዜ በቤተ መቅደስ አገልግሎት ላይ ነበረ:: ስለ ቤተ መቅደስ የመዝሙር አገልግሎት በኋላ ላይ እናያለን:: አሁን ግን በዘፀአት ምዕራፍ 15 ላይ ያለውን እናጠናለን::

እስራኤላዊያን ከግብጽ ምድር ሲወጡ እግዚአብሔር በግብጽ ሀገር የተለያዩ ታአምራት አድርጐዋል:: እንደገናም ከግብጽ ወጥተው ሲጓዙ ከፊት ለፊታቸው ቀይ ባህር፣ ከግራና ከቀኝ ተራራ ከኋላቸው ደግሞ የፈርዖን ሰረገሎች ወይም ወታደሮች ነበሩ:: እግዚአብሔር ቀይ ባህርን እንደ ጨርቅ በመጠቅለል እነዚህን ሰዎች በድንቅ ሁኔታ አሻግራቸዋል እነርሱም እግዚአብሔርን አመሰገኑ:: ዘፀ 15:1

ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር እስራኤላዊያንን ከግብጽ ምድር ያወጣበት ዋንኛው ምክንያት አምልኮን በተመለከተው በዘፀአት 8:1 “ከዚያም እግዚአብሔር አለው ወደ ፈረዖን ዘንድ ሂደህ እንዲ በለው ‘እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው’ “እኔን ***ያምልኩኝ ዘንድ*** ህዝቤን ልቀቅ .........” አመት:: እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባው ቁምነገር ቢኖር ግብፅ የጣኦታት አምልኮ የተንሰራፋባት ሀገር መሆኗ ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር ህዝቦቹ እንዲያመልኩት ፈረዖንን ልቀቅ ባለበት ጊዜ ፈረዖን ልቡን አደነደነ ምክንያቱም እግዚአብሔር አምኮን በተመለከተ ህዝቦቹ እንዲሳሳቱ አይፈልግም::

አሁን ትኩረታችን ወደ ዘፀ 15 ላይ እናትኩር:: በዚህ ክፍል እስራኤላዊያን ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር ሲያቀርብ ይታያሉ:: በቁጥር 19 እስከ 21 ላይ ላይ የአሮን እህት ነቢይቱ ማሪያምም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ሴቶችም ሁሉ ከበሮ ይዘው እያሸበሸቡ ተከተሏት ይላል:: ብዙዎች ይህንን ጥቅስ በመውሰድ ሽብሸባ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ያስፈልጋል ብለው ሲከራከሩ ይታያል:: ነገሩ እንዲህ ነው:: ማሪያም ከበሮ ከመውሰዷ በፊትና ሌሎችም እሷን ተከትሎ ከማሸብሸባቸው በፊት የተደረገ ድርጊት አለ:: እሱም እግዚአብሔር በድንቅ ሁኔታ ቀይ ባህርን ከፍሎ ማሻገራቸው ነው:: ይህ ደግሞ በክርስቶስ እና በሰይጣን (በእውነትና በሀሰት) መካከል የሚደረገው የታላቁ ተጋድሎ (ትንቅንቅ) ምሳሌ ነው:: ይህንን በተመለከተ patriarics and prophets የሚለው መጽሐፍ ገጽ 289 (በእንግሊዘኛው) እንዲህ ይነበባል:: “ያ መዝሙር (እስራኤላዊያን የዘመሩት) የአይሁድ ህዝብ ብቻ አልነበረም:: የጽድቅ ጠላት የሆነውን ሁሉ የሚያጠፋና በመጨረሻም የእስራኤልን አምላክ አሸናፊነትን የሚያመለክት ነበረ:: የጳጥሞው ነቢይ ያየው ነጭ ልብስ የለበሱና አሸናፊነትን ያገኙ የእግዚአብሔርን በገና ይዘው እሳት በተቀላቀለው በብርጭቆ ባህር ላይ ቆመው የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው የሙሴንና የበጉን መዝሙር ዘመሩ::”ራዕ 15:2-3. እንግዲህ ይህ ሽብሸባ የሚያሳየው ከዚህ አለም ስራችንን ጨርሰን ከጌታችን ከእየሱስ ጋር ስንገናኝ የምናሸበሽበው ሽብሸባ ነው:: ልብ እንበል ማሪያም ያሸበሸበችው ከዘመኑ ሽብሸባ ጋር በፍጽም አይገናኝም:: ጠቢቡ ሰለሞን እንዲህ ይላል “ለማልቀስ ጊዜ አለው ለመሳቅ ጊዜ አለው፤ ለሀዘን ጊዜ አለው ለጭፈራም ጊዜ አለው” መክ 3:4

ወገኖቼ ሆይ ይችህ ምድር በክርስቶስና በሰይጣን መካከል የሚደረገውን ታላቁ ተጋድሎ እያስተናገደች ባለችበት ጊዜ ሁላችንም በክርስቶስ ጐራ ሆነን ይህንን ጠላት መፋለም አለብን:: ወታደር ወደ ጦርነት ከመውጣቱ በፊት የተሰጠውን ተዕልኮ ለማሳካት እንዲያስችለው ተገቢውን ስልጠና በመውሰድ ጠላቱን መርታት አለበት:: በድል ወደ ሀገሩ ሲመለስ በደስታና በጭፈራ የሀገሩ መንግስት ይቀበለዋል:: ነገር ግን በጦርነት ላይ እያለ የሚደሰትና የሚጨፍር ወታደር የሚያጋጥመው ውጤት ሽንፈት ብቻ ነው:: “ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ ተጣለ እሱም ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው የአለምን ሁሉ የሚያስተው ነው፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላዕክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ... ስለዚህ ሰማያት ሆይ፣ በውስጣቸውም የምትኖሩ ሆይ ደስ ይበላችሁ፤ በምድርና በባህር ግን ወዮላችሁ::” ራዕ 12:9-12 ይህ ጥቅስ እንደሚያስተምረን በሰማይ ደስታ የሚሆንበት ሲሆን በምድር ላይ ደግሞ እየጸለዩ ክርስቶስን መጠበቅ ነው:: እንዲህ ስል ግን ‘ሁሉም ሰው የደከመ፣ ለእግዚአብሔር ደስ የያማሰኝ መዝሙር ማቅረብ አለበት’ ማለቴ አይደለም:: በእያንዳንዱ የህይወት ጉዟችን ውስጥ ለምናገኘው ድል እግዚአብሔርን የምናወድስበትና የምናመሰግንበት የምስጋናና የድል መዝሙር መሰዋት ማጣት የለብንም:: እስራኤላዊያንን ሲመራ የነበረው እግዚአብሔር በምድረበዳ እንዳያልቁ የመላዕክት ምግብ በሰማይ የተዘጋጀውን መገባቸው ከአለትም ውሃ አፈለቀላቸው ይህም ክርስቶስን ያመለክት ነበረ:: ነገር ግን ሙሴ ከሲና ተራራ ላይ ሳይወርድ በዘገየ ጊዜ እስራኤልያዊያን ተስፋ በመቁረጥ በግብፅ በነበሩበት ጊዜ ያዩትን የግብፃዊያን አማልክት እብዲሰሩላቸው አሮንን ጠየቁ:: አሮንም ለሚስቶቻቸው፣ ከወንድ ልጆቻቸው እንዲሁም ከሴት ልጆቻቸው የወርቅ ቀለበት ወስዶ በመሳሪያ በመቅረጽ የወርቅ ጥጃ

ሰራላቸው። ምን አይነት የሚያሳዝን ትዕይንት ነው? እነዚህ እስራኤላዊያን አንገተ ደንዳኖች ሆኑ እግዚአብሔርን ትተው ለማይሰማናለማይናገር ጥጃ እራሳቸውን አዋረዱ። ጭራሽ ከግብፅ ምድር ያወጣችሁ ይህ የወርቅ ጥጃ እንደሆነ አዋጅ ተነገረ እንደ እግዚአብሔር ሊያመልኩትም ቀን ቆረጡ። ዘፀ 32፥5